
# Guida pratica per i richiedenti protezione internazionale






SPRAR

Sistema di Protezione
per Richiedenti Asilo e Rifugiati

anci

Dipartimento per le libertà civili
e l'immigrazione

Commissione Nazionale
per il Diritto d'Asilo

**ማጣቀሻ**

ያላችሁበት ቦታ - የጣልያን አገር ካርታ

የአህጉራዊ ጥበቃ ጠያቂ ምን ዓይነት ሰው ነው?

የተባበሩት የአወሮጳ አገሮች ወስጥ ገብታቹሃል

የተባበሩት የአወሮጳ አገሮች ካርታ

የድፍን አለም ጥበቃ ጥያቄ የሚጠየቅበት ሁኔታ እንዴት እንደሚፈጸም

የድፍን አለም ጥበቃ ጥያቄ ደረጃዎች

- የድፍን አለም ጥበቃ ጥያቄ ማቅረብ (አንደኛ ደረጃ)
- ጉዳዩ ሲታይ (ሁለተኛ ደረጃ)
- የመንግስት ማስተናገጃ ማዕከል ወስጥ ልትገቡ ትችላላችሁ

የጥገኝነት ጠያቂዎች ማዕከል ወስጥ ያላችሁ መብቶች

እንደ ድፍን አለም ጥበቃ ጠያቂ ያላችሁ መብቶች

ሃገራዊ ስልጣን ያለው አካል ሊሰጣቸው የሚችል ወሳኔዎች (ሶስተኛ ደረጃ)፡

- የስደተኛ ፍቃድ ከተሰጣችሁ
- የሁለተኛ ደረጃ ጥበቃ ፍቃድ ከተሰጣችሁ
- በሰብአዊ ሁኔታዎች ምክንያት የመኖሪያ ፍቃድ ከተሰጣችሁ

ይግባኝ ማለት (አራተኛ ደረጃ)

የድፍን አለም ጥበቃ ፍቃዳችሁ ሲቋረጥ ወይም ሲሰረዝ


ወደ አገራችሁ በፍላጎት መመለስ

የቃላት ትርጉም ዝርዝር

አስፈላጊ የመገናኛ መረጃ

AMARICO

## ያላችሁበት ቦታ – የጣልያን አገር ካርታ



## የአህጉራዊ ጥበቃ ጠያቂ ምን ዓይነት ሰው ነው?

የአህጉራዊ ጥበቃ ጠያቂ ማለት ጥበቃ እንዲደረግለት ጠይቆ እንደስደተኛ መጠን ፍቃድ የሚሰጥ ውሳኔ ወይም ሌላ ዓይነት ጥበቃ እንዲሰጠው የሚጠብቅ ያለ ሰው ነው። ጣልያን ኣገር ውስጥ የሚገኙ የውጭ ኣገር ዜጎች ሁሉም የአህጉራዊ ጥበቃ ጥያቄ የማቅረብ መብት ኣላቸው።

## ስደተኛ ማለት

ማንኛውም ሰው ኣገሩ ውስጥ ወይም ሌላ ኣገር ውስጥ ወይም ያለ ዜግነት ይኖርበት ከነበረ ቦታ ተከትለው በሚገኙ ምክንያቶች እንዳይገደል ወይም እንዳይታሰር ፈርቶ ያመለጠ፣ የሚኖርበት ኣገር ውስጥ ለመኖር የማይችል ነው፣

- **በዘር** (ለምሳሌ በየቆዳህ ቀለም ይሁን ወይም በዘርህ የተወለድክበት ኣገር ውስጥ ለመኖር የማትችል ከሆንክ ንአብነት)፣

- **በሃይማኖት** (ለምሳሌ መንግስት የሚያንበትን ሃይማኖት ባለመከታተልህ ወይም መንግስት በማያምንበት ሃይማኖት በማመንህ)፣

- **በዜግነት** (ለምሳሌ በዜግነት ይሁን ወይም በቋንቋ ጥቂት ከሆኑ ማህበረሰቦች ኣባል ከሆንክ)፣

- **የአንድ ለየት ያለ ማህበረሰብ ኣባል በመሆንህ** (ለምሳሌ ከሰፊው ሕዝብ ለየት ብሎ ከሚኖር ማህበረሰብ ኣባል ከሆንክ፣ ለምሳሌ በግብረ ስጋ ግኑኝነት ወይ ጾታዊ ድርጊት፣ እንደዛውም ቤተሰብ፣ ባህል ወም ስራ)፣

- **በፖለቲካዊ ኣስተያየት** (ለምሳሌ በፖለቲካዊ ኣስተያየት ምክንያት፣ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ፣ ኣላቸው በተባለ ፖለቲካዊ ኣስተያየት ወይም የህሊና ተቃውሞ)፣

እንደዚህ ሆነው ብተጨማሪ ከኣገራቸው ወም የሚኖሩበት ከነበረ ኣገር መንግስት ጥበቃ ለማግኘት የማይፈልጉ ወይም የማይችሉ ሲሆን ነው።

ወከባ ማለት፣ ለምሳሌ የሕይወት ስጋት፣ ስቃይ፣ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ነጻነት ማጣት ወይም ከባድ የሆነ የሰብኣዊ መብቶችን የለመጠበቅ ነው።
የስደተኞች ፍቃድ እንዲሰጥህ የግድ ወከባ የደረሰብህ መሆን የለብህም።

እንደዛውም ኣንድ ሰው ወደ ኣገሩ ከተመለሰ ወደ ከባድ ኣደጋ ወይም ወከባ እንዲጋለጥ የሚያደርጉ የታወቁ ሁኔታዎች ካሉ፡ የስደተኞች ፍቃድ ሊሰጠው ይችላል።

የ "ስደተኛ" ትርጉም በኣንቀጽ 1 ስደተኞችን በሚመለከት የተደረገ የ 1951 የጀኒቫ ስብሰባ ይገኛል። ይህ እንደሚለው ስደተኛ ማለት ኣንድ ሰው *"ወከባ የሚያደርስበት እውቅ የሆነ ስጋት ኖሮት ይህ ደግሞ በዘሩ፣ ሃይማኖቱ፣ ዜግነቱ፣ ፖለቲካዊ ኣስተያየቱ ወይም የተወሰነ ማሕበረሰብ ኣባል በመሆኑ ሆኖ፡ እንደዛውም ከኣገሩ ውጭ ሆኖ ይህንን በሚመስል ፍራቻ ካለበት ኣገር ይጠቅመኛል ብሎ ጥበቃ ለመጠየቅ የማይፈልግ ወይም የማይችል ሲሆን፡ ወይም የማንም ኣገር ዜግነት የሌለው ሆኖ የሚኖርበት ከነበረ ኣገር ይህንን በሚመስሉ ምክንያቶች ወጥቶ በእንደዚህ ዓይነት ፍራቻ ወደዛ ለመመለስ የማይችልና የማይፈልግ ነው።"*

ባጠቃላይ፣ በኢኮኖሚያዊ ችግሮች ምክንያት እውነተኛ ቢሆኑም፣ ኣንዳንዴም በጣም ከባድ ሊሆኑ ይችላሉ፡ ነገር'ግን የስደተኞችን ፍቃድ የሚያስገኝ በቂ ምክንያት ኣይደለም።

**የሁለተኛ ደረጃ ጥበቃ** ማለት ኣንድ የየተባበሩት የኣውሮጳ ኣገሮች ዜጋ ያልሆነ ወይም ኣገር የሌለው ሆኖ የስደተኞች ፍቃድ ሊሰጠው ለማይችል ሰው የሚሰጥ ጥበቃ ነው። ይህም ይህ ሰው ወደ ኣገሩ ወይም ወደሚኖርበት የነበረው ኣገር ከተመለሰ የሚደርስበት እውቅ የሆነ ከባድ ኣደጋ ወይም ወከባ ሲኖር በተጨማሪም በዚህ ስጋት ምክንያት ካለበት ኣገር የጥበቃ ጥያቄ ለማቅረብ የማይችል ወይም የማይፈልግ ሲሆን ነው።

**የሰብኣዊ ድርጊት ጥበቃ** የፖሊስ ኣመራር በሰብኣዊ ምክንያቶች የመኖሪያ ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል። ይህ የጥገኝነት ጥያቄ የሚያቀርበው ሰውን በሚመለከት የክፍለ ሃገር ስልጣን ያለው ኣካል እንደ ድፍን ኣለም ጥበቃ ጠያቂ ባያየውም “ከባድ የሆነ ሰብኣዊ ምክንያት” ኣለ በሚልበት ሁኔታዎች ነው።

| **ምስጢርነት** |
|---|
| ባቀረባችሁት ድፍን ኣለም ጥያቄ ኣሰራርና የምርመራ ስራ ለሚሳተፉ ሰዎች የምታቀርቡላቸው መረጃ ላገራችሁ መንግስት ኣይሰጥም ወይ ወደዛ ኣይተላለፍም። |

**የተባበሩት የአውሮጳ አገሮች ውስጥ ገብታቹሃል**

ያላችሁት ጣልያን ኣገር ውስጥ ነው፣ ይህም ከተባበሩት የአውሮጳ ኣገሮች ኣንድ ኣባል በሆነች ኣገር ውስጥ ገብታቹሃል ማለት ነው።

በኣውሮጳ ሕግ መሰረት (**ሁለተኛው የዳብልን መምሪያ ሕግ**) ጥበቃ የምትጠይቁበት ኣገር መምረጥ ኣትችሉም። ቢሆንም ጥያቂያችሁ ብቃት ባለው ሁኔታ ለማየት የምትችል መሆን ኣለባት፣ ለምሳሌ፡

- ያለ ፍቃድ መጀመሪያ የገብችሁባት ኣገር፣
- **የመኖሪያ ፍቃድ ወይም የመግቢያ ፍቃድ** (**ቪዛ**) የፈቀድችላችሁ ኣገር፣
- የጣልያን ኣገር ውስጥ ለብቻችሁ ያላችሁና ከዕድሜ በታች ከሆናችሁ **ዘመዳችሁ በተከታታይ** በሚኖርበር ኣገር፣
- የስደተኞች ፍቃድ የተሰጠ ወይም የጥገኝነት ጥያቄ ያቀረበ ዘመድ በሚገኝበት ኣገር።

**ዘመድ** ማለት፡

- ባልሽ ወይም ሚስትህ፣
- ከናንተ ጋር ቋሚ ግንኙነት የለው ሰው፣ ይህም በምትቀበላችሁ ኣገር እንደጋብቻ የሚታይ ከሆነ ነው፣
- ትናንሽ ልጆቻችሁ፣ ይህም ንሮኣቸውን በሚመለከት እናንተ የምትጠብቁላቸውና ያላገቡ ሲሆኑ ነው፣
- ኣባታችሁ፣ እናታችሁ ወይም ከዕድሜ በታችና ያላገባችሁ ከሆናችሁ ተጠያቂ ሰው።

ከዚህ በላይ ተጠቅሰው ያሉት ባብዛኛው ጊዜ የሚያጋጥሙ ሁኔታዎች ናቸው፣ የመለኪያ ነጥቦች የሚሆኑ ሌሎችም ይገኛሉ። ከተጠራጠራችሁ ወይም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎን ሰራተኞችን ይጠይቁ።

ጣልያን ኣገር ውስጥ የድፍን ኣለም ጥበቃ ምርመራ ብቃት በሚመለከት ውሳኔ የሚሰጠው ማዕከሉ ውስጥ ባሉት ፖሊሶች ኣይደለም። ፖሊሶቹ ሰነዶችን ሮም ውስጥ ወደሚገኘው የውስጣዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ("የዳብልን ክፍል") ቢሮ ጉዳዩ ወደሚመለከተው ክፍል ያስተላልፉታል። ይህ ክፍል በቀረበው መረጃ መሰረት ውሳኔ ይሰጣል። ቢሆንም ትክክለኛ ውሳኔ እንዲሰጥ ኣስፈላጊ የሆነው ሁሉም መረጃ መቅረብ ኣለበት። ማስታወስ የለባችሁ ነገር፡ ወደ "የዳብልን ክፍል" የሚተላለፍ መረጃ ሁሉም የማወቅና፣ ስሕተት ቢኖር ደግሞ የማስተካከል መብት ኣላችሁ።
ጣልያን ኣገር የጥገኝነት ጉዳያችሁን ለማየት ብቃት ያላት እንደሆነች ለመወሰን ስራ በሚካሄድበት ሰዓት፡ ጣልያን ኣገር ውስጥ ያላችሁበት ሁኔታ እንደ ጥገኝነት ጥያቄ ኣቅራቢ ይሆናል።

የድፍን ኣለም ጥበቃ ጥያቂያችሁ ማየት ያለባት ኣገር የሚገልጽ ውሳኔ ከተሰጠ፣ የዳብልን ክፍል ውሳኔ ከተሰጣችሁ ጊዜ ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ ይግባኝ ማለት ትችላላችሁ።

ሕጉ እንደሚለው ጠበቃ መቅጠር ትችላላችሁ። ጠበቃውን መክፈል የማትችሉ ከሆነ፣ ከክፍያ ነጻ የሆነ ሕጋዊ እገዛ እንዲሰጣችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ (ይህ በመንግስት የሚከፈል ይሆናል)።

## የተባበሩት የአውሮጳ አገሮች ካርታ




© የአውሮጳ ማሕበረሰብ 1995-2007

የተባበሩት የአውሮጳ አገሮች አባሎች እንደሚከተሉ ናቸው፡
ኦስትርያ፣ በልጂየም፣ ቡልጋርያ፣ ሳይፐረስ፣ ዴንማርክ፣ ኤስቶንያ፣ ፊንላንድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ግሪክ፣ አየርላንድ፣ ጣልያን አገር፣ ላትቭያ፣ ሊትወንያ፣ ላክሰምበርግ፣ ማልታ፣ ሆላንድ፣ ፖላንድ፣ ፖርቱጋል፣ እንግሊዝ አገር፣ ቸኮዝሎቫክያ ረፓብሊክ፣ ሮሜንያ፣ ስሎቫክያ፣ ስሎቬንያ፣ ስፐይን፣ ስዊድን፣ ሃንጋሪ።

**የድፍን ኣለም ጥበቃ ጥያቄ የሚጠየቅበት ሁኔታ እንዴት እንደሚፈጸም**

የድፍን ኣለም ግላዊ ጥበቃ ጥያቄ መቅረብ ያለበት ቦታ፡

- ድንበሩ ጋር ያሉት ፖሊሶች፣ ይህ ጣልያን ኣገር መጀመሪያ እንደገባችሁ ነው፣
- ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ - ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ የስደተኞች ቢሮ፣ ጣልያን ኣገር ውስጥ ገብታችሁ ከሆነ።

የድፍን ኣለም ጥበቃ ጥያቄያችሁ በሚመለከት ሃገራዊ ስልጣን ባለው ኣካል ውሳኔ እስከሚሰጣችሁ ኣገር ውስጥ የመቆየት ፍቃድ ኣላችሁ።

**ኣስታውሱ፡** ከፍተኛው ኣስተዳዳሪ ባቀረባችሁት የድፍን ኣለም ጥበቃ ውሳኔ እስከሚሰጥ የት እንደምትቆዩ ይወስናል።

የድፍን ኣለም ጥበቃ ጥያቂያችሁ በተገቢ ሰዓት ባለመቅረባችሁ ብቻ ተቀባይነት ማጣት ኣይችልም። ጥያቂያችሁን ልታቀርቡበት የምትችሉ የጊዜ ገደብ የለውም።

ስራው በሚካሄድበት ጊዜ ከ ዩ ኤን ኤች ሲ ኣርና (UNHCR) ሌሎች የድፍን ኣለም ጥበቃ ጥያቄ ላቀረቡ እንክብካቤ ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር መገናኘት ትችላላችሁ።

እንተተጠራችሁ፣ ሃገራዊ ስልጣን ካለው ኣካል ዘንድ መቅረብ ኣላችሁ። ፓስፖርትዎና ሌሎች ከጥያቂያችሁ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰነዶች ሁሉም ማስረከብ ኣላችሁ።

**ኣድራሻችሁን በምትቀይሩበት ሰዓት ሳትረሱ ፖሊስን ማሳወቅ ኣለባችሁ፣ ባታደርጉ ወደ እናንተ የሚላኩት ደብዳቤዎች ባይደርስዋችሁም ወደ መጨረሻ የሰጣችሁት ኣድራሻ እንደደረሰ ይታሰባል።**

ሃገራዊ ስልጣን ያለው ኣካል ጉዳያችሁን ይሰማል። ደብዳቤዎችም በፖሊስ ጣቢያ በኩል ወደ እናንተ ይልካል።

በጤና ችግር ምክንያት የቃለ መጠይቅ ቀጠሮ ማክበር ካልቻላችሁ የቀጠሮውን ቀን መቀየር ይቻላል። የቃለ መጠይቅ ቀጠሮውን ለማክበር ያላስቻላችሁ ከባድ የጤና ችግር ካለ ባሓኪም የተረጋገጠ መሆን ኣለበት።

**አስታውሱ**

– በማንኛውም ጉዳይ በተከታታይ የመምሪያ መረጃ ይሰጣችሁ ከነበረ፣ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ካልመጣችሁና የቃለ መጠይቁ ቀን እንዲቀየርላ ያልጠየቃችሁ ከሆነ፡ ስልጣን ያለው አካል ውሳኔ የሚሰጠው ቀርበውለት ባሉት ሰነዶች መሰረት ብቻ ይሆናል።

– ነገር'ግን ስልጣን ያለው አካል ጉዳያችሁን የሚያይበት ስነ ስርዓት በሚመለከት ያልተነገራችሁ ከሆነና ስልጣን ያለው አካል የድፍን ኣለም ጥ ጥያቂያችሁን በሚመለከት ውሳኔ ያልሰጠ እንደሆነ <u>ኣንድ</u> ኣዲስ ተጨማሪ ቀጠሮ ሊሰጣችሁ ይችላል። ይህም ቀጠሮ ማክበር ያላስቻላችሁ ነገር ከተፈታ ጊዜ ጀምሮ በ<u>10 ቀናት</u> ውስጥ መሆን ኣለበት።

ይህ የተመሰረተው በኣዲሱ ድፍን ኣለም ጥበቃ ኣሰራር ነው።

AMARICO

## የድፍን ኣለም ጥበቃ ጥያቄ ደረጃዎች

### የድፍን ኣለም ጥበቃ ጥያቄ ማቅረብ (ኣንደኛ ደረጃ)

የድፍን ኣለም ግላዊ ጥበቃ ጥያቄ መቅረብ ያለበት ቦታ፡
ድንበሩ ጋር ያሉት ፖሊሶች፣ ይህ ጣልያን ኣገር መጀመሪያ እንደገባችሁ ነው፣
ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ - ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ የስደተኞች ቢሮ፣ ጣልያን ኣገር ውስጥ ገብታችሁ ከሆነ።

ኣስታውሱ፡ ልጅ ካላችሁ ጉዳያችሁ ያላገቡ፣ ከዕድሜ በታች የሆኑና በጣልያን ኣገር ውስጥ የሚገኙ ልጆቻችሁን ያጠቃልላል።

ወደ ጣልያን ኣገር ያለ ፍቃድ (ቪዛ) ገብታችሁ እንደሆነ፣ የጣልያን ኣገር ሕግ **ማንነትን ለይቶ የማወቅ ስራ** ያካሂዳል። ይህም በፖሊስ የሚደረግ ሆኖ የጥገኝነት ጉዳያችሁ ከመጀመሩ በፊት ማንነታችሁ መታወቅ ስላለበት ነው።

ይህንን በሚመለከት ፖሊስ ጣቢያ ቢሮ ዘንድ የሚደረግላችሁ ቀጠሮ መቼ እንደሆነ ይነገራቹሃል። በዚህኛው ቀን ኣንድ ፖሊስ፡ ኣስፈላጊ ከሆነም የመጀመሪያ ቋንቋችሁን የሚናገር ኣስተርጓሚ ወይም ሃሳብችሁን ለመግለጽ የምትችሉበት ቋንቋ የሚናገር ኣስተርጓሚ ይኖራል።

ፖሊሱ ፎቶና የጣን ኣሻራችሁን ይወስዳል (“*Fotosegnalamento*” = ማንነትን ለይቶ የማወቅ ስራ)

ከዚህ ቀጥሎ ጉዳያችሁን እውቅ ለማድረግ ቀጠሮ ይሰጣቹሃል፣ በዛን ሰዓት “በጀኔቫ ስብሰባ መሰረት ልማዳዊ የሆነው የስደተኞች ደረጃ የሚገልጽ የሚሞላ ወረቀት (ልማዳዊ ወረቀት C/3) ይሞላል”። የሚቀርቡላችሁ ጥያቄዎች (ስማችሁ፣ ያባታችሁ ስም፣ የተወለዳችሁበት ዕለት፣ የተወለዳችሁበት ቦታ፣ ዜግነታችሁ) እንደዛውም ቤተሰቦቻችሁን በሚመለከት (የወላጆችና ያባት ስም፣ የባልሽ/ሚስትህ ስምና ያባት ስም፣ የልጆቻችሁንና ያባት ስም፣ እንደዛውም ቤተሰቦቻችሁ የሚኖሩበት ቦታ)፣ በተጨማሪ የምትጠየቁት፡

- ከኣገራችሁ እስከ ጣልያን ኣገር ድረስ ያለው የጉዞ መንገድን መግለጽ (ይህም የተነሳችሁበት ቀን፣ ጉዞው የፈጀባችሁ ጊዜ፣ በምን እንደተጓዛችሁ)፣
- ከኣገራችሁ የወጣችሁበት ምክንያት ባጭሩ መግለጽ፣
- እነዚህ ምክንያቶችን ባጭሩ መጻፍ፡ ይህንን በመጀመሪያ ቋንቋችሁ ወይም ሃሳባችሁን ለመግለጽ በምትችሉበት ቋንቋ ለመጻፍ ትችላላችሁ።

**ኣስታውሱ፡** የማንበብ ወይም የመጻፍ ችግር ካላችሁ ሰራተኞቹን ወይም ለፖሊስ ይናገሩ።

***ፖሊሶቹ ኣንደኛውን ልማዳዊ የሚሞላ ወረቀት C/3 ኣስቀርተው ኣንድ ቅጂ ይሰጣቹሃል።***

ቃለ መጠይቅ በሚደረግበት ሰዓት ለፖሊስ የሚሰጠው መረጃ ሁሉም ምስጢራዊ ነው፡
- ወደ የኣገራችሁ መንግስት ሊተላለፍ ኣይችልም፣
- ማዕከሉ ውስጥ ወይም ከዛ ውጪ ወዳሉ ሰዎች ሊተላለፍ ኣይችልም።

***ልማዳዊ ከሆነው የሚሞላ ወረቀት C/3 በላይ ግላዊ ታሪካችሁን የሚገልጽ ተጨማሪ ገጽ ለመጻፍ ትችላላችሁ። ይህም በግድ በጣልያንኛ ቋንቋ መጻፍ የለበትም፣ በመጀመሪያ ቋንቋችሁ ለመጻፍ ትችላላችሁ።***

ፖሊሶቹ ወረቀት እንዳላችሁና እንደሌላችሁ ይጠይቃቹሃል (ይህም የመታወቂያ ወረቀት፣ ፓስፖርት፣ ኤል ኣይ ፒ (ልዩ የመግቢያ ፍቃድ) የፓርቲ ኣባልነት መታወቂያ፣ የምስክር ወረቃቅቶች)። ፓስፖርትን የሚያካትቱ ወረቃቅቶች ካላችሁ ለፖሊስ መስጠት ኣለባችሁ፣ ቅጂ ይወስዳሉ።
ፕሊሶቹ በኩር ቅጂውን ኣስቀርተው ኣንድ ማህተም ያለው ቅጂ (“የተመላሽ መዝገብ”) ይሰጣቹሃል።

**የመስተንግዶ ጥያቄ ማቅረብ**
ራሳችሁን የምትችሉበት ዓቅም ከሌላችሁ እንደዛውም የመንግስት መቀበያ ማዕከል ውስጥ የሌላችሁ ከሆናችሁ፣ ፖሊስ ከኣስተዳደር ጋር ተገናኝተው በኣካባቢው ኣካሎች የሚካሄዱ የጥገኝነት ጠያቂዎችና ስደተኞች ማዕከሎች (Sprar) ኣንድ ውስጥ መስተንግዶ እንዲደረግላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ።

AMARICO

**አስታውሱ**

- ጉዳያችሁን ስታቀርቡ የፖሊስ ቢሮ መከተል ስላለባችሁ ነገሮች፣ ጉዳዩ በሚካሄድበት ሰዓት ያላችሁ መብቶችና ተጠያቂነት፣ እንደዛውም ጉዳያችሁን የሚደግፉ ኣስፈላጊ ለማቅረብ ያላችሁ ጊዜና መንገዶች ይነግራቹሃል፣
- ዋናው ቢሮ የድፍን ኣለም ጥበቃ ጥያቂያችሁን እንደተቀበለ፣ የሰጣችሁት ቃል በሚመለከት ዘገባ ኣዘጋጅተው ከሰነዱ ጋር ያያይዙታል። ይህንን ዘገባ ትክክል መሆኑ ኣረጋግጣችሁ ከፈረማችሁ ቀጥሎ፣ የዛና የሰነዱ ቅጂ ይሰጣቹሃል፣
- ሃገራዊ ስልጣን ያለው ኣካል የስደተኞች ፍቃድ እንዲሰጣችሁ የሚያስችል በቂ መረጃ ካለው ቃለ መጠይቅ እንዳይደረግላችሁ ውሳኔ መስጠት ይችላል። እንደዛውም ለመቅረብ የማትችሉ ከሆነ ኣካሉ ቃለ መጠይቅ ላያደርግላችሁ ወይም ለሌላ ቀን ሊቀይረው ይችላል፣
- ለሌላ ቀን እንዲቀየርላችሁ ሳትጠይቁ ቃለ መጠይቁ በሚደረግበት ሰዓት ባትገኙ ስልጣን ያለው ኣካል በቀረቡለት ሰነዶች መሰረት ውሳኔ ይሰጣል፣
- የድፍን ኣለም ጥበቃ ጥያቂያችሁ ስራ ውስጥ ለሚሳተፉ ኣካሎችና ሰራተኞች የምትሰጡት መረጃ ለኣገራችሁ መንግስት ኣይገለጽም፣
- ከኣገራችሁ የወጣችሁበት ምክንያት በሙሉ መግለጽና መጻፍ ኣስፈላጊ ነው፣
- ሃሳባችሁን የመግለጽና የመጻፍ ችግር ካላችሁ፣ ለማስታወስ የማትችሉት ነገር ካለ፣ ስታስትውሱና ማብራሪያ ስትሰጡ ድካምና ጭንቀት የሚሰማችሁ ከሆነ ወይም ማብራሪያ ለመስጠት ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልጋችሁ ከሆነ እባክዎን ቃለ መጠይቅ በሚደረግበት ሰዓት ያስታውቁ፣
- ከኣገራችሁ ያመለጥኩባቸው ምክንያቶች በሙሉ ለመግለጽ/ ወይም ለመጻፍ በቂ ጊዜ ከሌላችሁ፣ ኣስፈላጊ የሆኑትን ምክንያቶች ሰጥታችሁ መረጃው ጎደሎ መሆኑ ያስታውቁ፣
- ከኣገራችሁ ያመለጥኩባቸው ምክንያቶች በሙሉ ለመግለጽ ካልቻላችሁ፣ ፖሊስ ቢሮ ዘንድ ክነበረው ቀጠሮ በኋላ ተጨማሪ ቃል ጽፋችሁ ኣስረክቡ፣
- ከፖሊስ ወይም ከኣስተርጓሚ ጋር በሚደረገው ስብሰባ የተባለው ነገር እንዲብራራላችሁ የምትፍልጉ ወይም ኣጠራጣሪ ነገር ካለ፣ በተሻለ መጠን ለመጻፍና ለማስታወስ እገዛ የሚያስፈልጋችሁ ከሆነ፣ እነዚህን ነጥቦች ጠበቃችሁን ያስታውቁት፣
- ሳትረሱ ሁሌ ለፖሊስ የምታስረክብዋቸው ሰነዶች ቅጂ ያስቀሩ።

የጥገኝነት ጉዳይን በሚመለከት የሚደረጉት ግንኙነት ሁሉም (ለምሳሌ ፖሊስ ወይ ስልጣን ያለው ኣካል ዘንድ የሚደረገው ስብሰባ፣ ወረቀት የማቅረብ ጥያቄ፣ ወደ ሌላ ኣገር የማስተላለፍ ጉዳይ፣ ስልጣን ያለው ኣካል የሚሰጣቸው ውሳኔዎች) በመጀመሪያ ቋንቋችሁ ይደረጋሉ፣ ይህ በቂ ካልሆነ በእንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ስፓኒሽ ወይም ዓረብኛ ሆኖ እናንተ ባደረጋችሁት ምርጫ መሰረት ይሆናል።

AMARICO

**ጉዳዩ ሲታይ (ሁለተኛ ደረጃ)**

የድፍን ኣለም ጥበቃ ጥያቄ በሚመለከት ውሳኔ የመስጠት ስራ የሚደረገው ኣራት ኣባሎች ባሉበት **ሃገራዊ ስልጣን ያለው ኣካል የድፍን ኣለም ጥበቃ ፍቃድ** በሚባል ነው፡

- 2 የውስጣዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኣባሎች
- 1 የኣስተዳደር ወኪል (ወይም የኣውራጃ)
- 1 የ ዩ ኤን ኤች ሲ ኣር ወኪል (UNHCR)

ሕጉ እንደሚለው ስልጣን ያለው ኣካል ጋር የሚደረገው ስብሰባ (ወይም ቃለ መጠይቅ) ዘንድ እንድትገኙ ከፖሊስ የመጥሪያ ደብዳቤ መላክ ኣለበት።

ስብሰባ በሚደረግበት ሰዓት ቋንቋችሁን የሚናገርና የሚባሉት ነገሮችን የሚያስተረጉም ኣስተርጓሚ ይኖራል።

በጤና ችግር ምክንያት የስብሰባው ቀን እንዲቀየርላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ። ይህም ማስረጃ ያስፈልገዋል። ወይም በሌሎች ከባድ ምክንያቶች ቃለ መጠይቁ ስልጣን ካለው ኣካል ኣባሎች ከኣንዳቸውና ከእራስዎ ጋር ተመሳሳይ ጾታ ካለው ሰው ጋር እንዲደረግላችሁ መጠየቅ ችላላችሁ።

እንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ባሉበት ሰዓት የማዕከሉን ሰራተኞች ያስታውቁ።

ስብሰባው ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በ **30 ቀናት** ውስጥ ይካሄዳል። ኣካሉም ከዚህ ቀጥለው ባሉት ሶስት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

ኣስታውሱ፡

- ጉዳያችሁ በግልጽ እውቅ ከሆነና እናንተም ተጎጂ ሆናችሁ ከተገኛችሁ ጥይቂያችሁ **የቀዳሚነት ምርመራ** ይደረግለታል።
- ስልጣን ያለው ኣካል የስደተኛ ፍቃድ ካላችሁ ወይም ካሁን በፊት ተቀባይነት ኣጥታችሁ ሆኖ ኣዳዲስ ማስረጃዎች ወይም ያጋጠማችሁ ነገር ሳይኖር የቀረባችሁ እንደሆነ ጥያቂያችሁ **ተቀባይነት እንደሌለው ይገለጻል።**

ስልጣን ያለው ኣካል  የቀጠሮውን ቀን ለመቀየር እንዲወስን የሚያስችሉት ነጥቦች፡

- ለመወሰን ተጨማሪ ጊዜ ወይም ሰነዶች ሲያስፈልጉት፣
- በቀጠሮ ሰዓት ልትገኙ የማትችሉ ከሆናችሁ፣
- ከኣስተርጓሚ ጋር ያለመግባባት ሲኖር።

ስልጣን ያለው ኣካል የሚያቀርባቸው የጥያቄ ዓይነቶች፡

- እርስዎንና ቤተሰብዎን የሚመለከቱ መረጃዎች፣
- ጉዞውን በሚመለከት፣
- ኣገርዎን ለቀው እንዲወጡ ያርደረጓችሁ ምክንያቶች፣
- ወደ ኣገራችሁ ለመመለስ የማትፈልጉባቸው ወይም የማትችሉባቸው ምክንያቶች።

**ማስታወስ ያለባችሁ፡**

- ከዕድሜ በታች ከሆናችሁ ጉዳያችሁ ስልጣን ባለው ኣካል የሚታየው ከወላጆቻችሁ ኣንዳቸው ወይም ተጠያቂነት ባለው ሰው ዘንድ ነው፣
- ስልጣን ባለው ኣካል ዘንድ እንደቀረባችሁ ሃሳባችሁን በመጀመሪያ ቋንቋችሁ የመግለጽ መብት ይኖራቹሃል፣
- ከኣስተርጓሚው ጋር የመግባባት ችግር ቢኖር፣ እባክዎን ስልጣን ያለው ኣካልን ያሳውቁት፣
- ጉዳያችሁ ሲታይ የሚሰጠው መረጃ በሚስጢራዊ መልክ የሚያዝ ነው፣
- በሕጉ መሰረት ጉዳያችሁ በሚታይበት ሰዓት የጠበቃ እገዛ ይሰጣቹሃል። ጉዳያችሁ ከሚታይበት ቀን በፊት ከጠበቃችሁ ጋር በመገናኘት ምክር ለማግኘት እንድትችሉ ማዕከል ውስጥ የሚገኘውን የሕግ ሰራተኛን ያስታውቁት፣
- ጉዳያችሁ ከሚታይበት ቀን በፊት ሰነዶችና ቃላችሁን የያዘ ደብዳቤ ስልጣን ያለው ኣካል ዘንድ መላክ ትችላላችሁ።
- ታሪካችሁን በሙሉና ዘገባን በዝርዝር በሚሰጥ መልክ ማቅረብ ኣስፈላጊ ነው፣
- ሃሳባችሁን የመግለጽ ችግር ካላችሁ፣ ለማስታወስ የማትችሉ ከሆናችሁ ወይም ችግር ካላችሁ፣ ስታስታውሱ ወይም ስታብራሩ መጥፎ ነገር የሚሰማችሁ ከሆነ ጉዳያችሁ በሚታይበት ሰዓት ማስታወቅ ኣለባችሁ፣

- የአካል ወይም ስነ ልቦናዊ ችግር ካላችሁ ስልጣን ያለው አካልን ያስታውቁት። እገዛ የሚያስፈልጋችሁ ከሆነ ማዕከሉ ውስጥ ባሉት ሰራተኖች ይሰጣቹሃል፣
- ጉዳያችሁ በሚታይበት ሰዓት የምትሰጡት ቃል ወረቀት ላይ (መዝገብ) ይጻፋል፣ ይህንንም መፈረም ይኖርባቹሃል፣ ጉዳያችሁ ከታየ በኃላ ሰነዱ ይሰጣቹሃል። ወረቀቱ ላይ **ከመፈረማችሁ በፊት የተጻፈው እንዲተረጎምላችሁ ይጠይቁ**፣ ይህም የሰጣችሁት ማብራሪያ በትክክል እንደተጻፈ ለማረጋገጥ ነው። አልፈርምም ካላችሁ ምክንያቱን መግለጽ ይኖርባቹሃል። አልፈርምም በማለታችሁ ስልጣን ያለው አካል የድፍን አለም ጥበቃ ጥያቂያችሁን በሚመለከት ውሳኔ መስጠቱ አይቀርም።

**ከዕድሜ በታችና ጣልያን አገር ውስጥ የላችሁ ከሆናችሁ፡**

- ስልጣን ያለው አካል ጉዳያችሁን የሚያየው ከወላጆቻችሁ አንዳቸው ወይም ተጠያቂነት ባለው ሰው ዘንድ ነው፣
- ስልጣን ያለው አካል በቀረቡት ሰነዶችና ለፖሊስ በሰጣችሁት ቃል መሰረት **ፍቃድን የመስጠት ውሳኔ** ከሰጠ **ጉዳያችሁ ወደሚታይበት ስነ ስርዓት እንድትቀርቡ ላይጠራችሁ ሊወስን ይችላል**።

ጥቅም ላይ ለመዋል የሚችል ደረጃ

**የመንግስት ማስተናገጃ ማዕከል ውስጥ ልትገቡ ትችላላችሁ**

ለድፍን ኣለም ጥበቃ ጠያቂዎች የሚሆን የመንግስት ማስተናገጃ የጥገኝነት ማዕከል ውስጥ ልትገቡ ትችላላችሁ፡

1. **ጥያቄ ያቀረባችሁት ከድንበር ጠባቂዎች እያመለጣችሁ ወይም ለማምለጥ እየሞከራችሁ ወይም ከዛ በኃላ ተይዛችሁ እንደሆነ፣**

2. **ጥያቄ ያቀረባችሁት ያለፍቃድ እያላችሁ ተይዛችሁ እንደሆነ፣**

**በጣልያን ኣገር ሕግ መሰረት ከማዕከሉ ያለፍቃድ መውጣት የጥገኝነት ጥያቂያችሁን ያስቀራል ማለት ኣይደለም፣ ቢሆንም ስልጣን ያለው ሃገራዊ ኣካል ለድፍን ኣለም ጥበቃ ያቀረባችሁትን ጥያቄ በሚመለከት የቀረቡትን ሰነዶች በማየት ውሳኔውን ይሰጣል።**

ውጭ ለመውጣት ወይም ማንኛውን ሌላ ነገር ለማድረግ እንደዛውም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጋችሁ፣ ሁሌ ማዕከሉ ውስጥ ለሚገኘውን የሕግ ሰራተኛ ይጠይቁት።

1ኛና 2ኛ ነጥቦችን በሚመለከት የጥገኝነት ጥያቄ ካቀረባችሁት ቀን ጀምሮ ማዕከሉ ውስጥ **ከ35 ቀናት** በላይ ኣትቆዩም።

***ወይም***

***3 – የመታወቂያ ወይም የጉዞ ሰነድ የሌላችሁ ከሆናችሁ ወይም ለማታለል የተሰሩ ሰነዶች ኣሳይታችሁ እንደሆነ፣ ማንነታችሁ ወይም ዜግነታችሁ ለማወቅ ኣስፈላጊ በሚሆንበት ሰዓት፣***

**ኣስታውሱ** እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲኖር ኣስፈላጊ ድርጊቶች እስከሚፈጸሙ ከ20 ቀናት ለማይበዛ ጊዜ ነው የምትያዙት።

**በጣልያን ኣገር ሕግ መሰረት ከማዕከሉ ያለፍቃድ መውጣት የጥገኝነት ጥያቂያችሁን ያስቀራል ማለት ኣይደለም፣ ቢሆንም ስልጣን ያለው ሃገራዊ ኣካል ለድፍን ኣለም ጥበቃ ያቀረባችሁትን ጥያቄ በሚመለከት የቀረቡትን ሰነዶች በማየት ውሳኔውን ይሰጣል።**

ውጭ ለመውጣት ወይም ማንኛውን ሌላ ነገር ለማድረግ እንደዛውም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጋችሁ፣ ሁሌ ማዕከሉ ውስጥ ለሚገኘውን የሕግ ሰራተኛ ይጠይቁት።

***ማዕከሉን ለቆ መውጣት፡*** *በሕግ መሰረት ከማዕከሉ በቀን መውጣት ትችላላችሁ። በተጨማሪም በሌሎች ሰዓታት ለመውጣት ፍቃድ እንዲሰጣችሁ ኣስተዳዳሪውን ለመጠየቅ ትችላላችሁ። ከባድና ግላዊ፣ የጤና ወይም የቤተሰብ ችግር ካላችሁ፣ ወይም በድፍን ኣለም ጥበቃ ጥያቂያችሁ ምክንያት ረዘም ላለ ጊዜ ለመውጣት ፍቃድ ሊሰጣችሁ ይቻላል።*

የሚያጠራጥራችሁ ነገር ካለ ወይም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጋችሁ፣ የማዕከሉ መምሪያን ያንቡ ወይም ሰራተኛን ያነገግሩ።

**ባጠቃላይ፡**

- በ1፣ 2ና 3 ባሉ ነጥቦች፣ የፖሊስ ባለ ስልጣን የድፍን ኣለም ጥበቃ ጥያቂያችሁን ተቀብሎ የድፍን ኣለም ጥበቃ ጠያቂ መሆናችሁን የሚገልጽ ወረቀት ሰጥቶ ወደ ድፍን ኣለም ጥበቃ ጠያቂዎች ማዕከል እንደምትወሰዱ ያደርጋል። ይህ የመኖሪያ ፍቃድ ወረቀት እንዳልሆነ ኣትርሱ።

- እዛ የምትቆዩበት ጊዜ ካለቀ ለሶስት ወራት የሚያገለግል ጊዚያዊ የመኖሪያ ፍቃድ ይሰጣቹሃል። ይህ የጥያቂያችሁ ውሳኔ

- እዛ የምትቆዩበት ጊዜ እንዳለቀና የድፍን ኣለም ጥበቃ ፍቃድ እንደተሰጣችሁ ማዕከሉን ለቃችሁ መውጣት ኣለባችሁ። ጣልያን ኣገር ውስጥ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ መንቀሳቀስ ትችላላችሁ። በዚህ ሰዓት እንቅስቃሲያችሁን በሚመለከት ለፖሊስ ቢሮ የት እንደምትኖሩ ሁሌ ማሳወቅ ኣለባችሁ። ይህ የሚላኩላችሁ ደብዳቤዎችና ስልጣን ያለው ኣካል ዘንድ መቅረባችሁን በሚመለከት ኣስፈላጊ ነው። ማዕከሉን ለቃችሁ ስትወጡ ቀጥሎ መስተንግዶ ሊደረግላችሁ ስለሚቻልበት ቦታ ለማወቅ ሰራተኞቹን ያነጋግርዋቸው።

- ጉዳያችሁን በሚመለከት የድፍን ኣለም ጥበቃ ጥያቄ ካቀረባችሁት ቀን ጀምሮ ለ6 ወራት ውሳኔ ካልተሰጠ፣ ለ6 ወራት የሚያገለግልና የጉዳያችሁ ውሳኔ እስከሚሰጣችሁ እንድትሰሩ የሚፈቅድላችሁ የመኖሪያ ፍቃድ የማግኘት መብት ኣላችሁ።

- ስልጣን ያለው ኣካል ግላዊ ጉዳያችሁ ከማየቱ በፊት ጥያቄያችሁን ለማስቀር ከወሰናችሁ፣ እንደዛ ማድረጋችሁ ሃገራዊ ስልጣን ያለው ኣካልን ይነገረዋል።

**ኣስታውሱ** በኣውሮጳ ሕግ መሰረት ውሳኔ እንዲሰጣችሁ በምትጠብቁበት ሰዓት ከጣልያን ኣገር መውጣት ኣትችሉም።
ወደ ሌላ የኣውሮጳ ኣገር ከሄዳችሁ፣ ከሕግ ውጭ በሆነ ስጋት ልትገኙ ትችላላችሁ።
ወደ ሌላ የኣውሮጳ ኣገር ሄዳችሁ ጥገኝነት ከጠየቃችሁ፣ ወደ ጣልያን ኣገር ልትመለሱ ትችላላችሁ ምክንያቱም የድፍን ኣለም ጥበቃ ጥያቄያችሁን በሚመለከት ውሳኔ የመስጠት ተጠያቂነት ያላት ኣገር ስለሆነች ነው (የዳብልን ሁለተኛ መምሪያ)።

## የጥገኝነት ጠያቂዎች ማዕከል ውስጥ ያላችሁ መብቶች

በጣልያን ኣገር ሕግ መሰረት፡
- ሕክምናና የመጀምሪያ እርዳታ የማግኘት **መብት ኣላችሁ**
- ወንዶችና ሴቶች ለየብቻቸው የሚኖሩበት ቦታ የማግኘትና ከዘመዶቻችሁ ጋር ኣብራችሁ የመትኖሩበት ቦታ የማግኘት **መብት ኣላችሁ**
- ከዚህ ተከትለው ያሉት መጥተው እንዲያያችሁ የሚያስችል **መብት ኣላችሁ**፡

- የ ዩ ኤን ኤች ሲ ኣር (UNHCR) ወኪሎች፣
- ጠበቃዎች፣
- ስልጣን ያላቸው የስደተኞች ታዛቢዎች፣
- ኣስተዳዳሪውን ፍቃድ ጠይቀው የተሰጣቸው ዘመዶቻችሁ ወይም የጣልያን ኣገር ዜጎች።

በተጨማሪም፡
- የናንተ ዓይነት ጾታ የሆነ ሰራተኛ ይሻለኛል ካላችሁ፡ እንደዛ ከሆኑ ሰራተኞች መነጋገር ወይም መጥተው እንዲጠይቋችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ። እንደዛውም ሰራተኞቹ ስልጣን ባለው ኣካል ዘንድ ቃለ መጠይቅ ሲደረግላችሁ ኣንድ የናንተ ዓይነት ጾታ የሆነ እንዲገኝ መጠየቅ ተቀባይነት ኣለው፣
- ሰራተኞቹን ኣመጋገብን በሚመለከትና ሌሎች ልዩ ነገሮች ለምሳሌ ሃይማኖትን በሚመለከት ምርጫችሁን መናገር **ትችላላችሁ።**

**<u>ለየት ያለ ሁኔታ ካጋጠማችሁ</u>**
ለምሳሌ፣

- እርግዝና ካጋጠመ፣
- ኣካላዊ ችግር ካላችሁ፣
- በዕድሜ የገፉችሁ ከሆናችሁ፣
- በሽተኛ ከሆናችሁ፣
- ኣካላዊ ወይም ስነ ልቦናዊ ወከባ የደረሳችሁ ከሆናችሁ፣
- ስቃይ ወይ መጥፎ ኣያያዝ ያጋጠማችሁ ከሆናችሁ፣
- የጾታዊ ውክቢያ የደረሳችሁ ከሆናችሁ፣

ኣስፈላጊ እገዛ እንዲሰጣችሁ ማዕከሉ ውስጥ ያሉትን ሰራተኞችን መንገር ትችላላችሁ። የደረሰባችሁን ከባድና የሚያስቃዩ ኣጋጣሚዎች ከመናገር ኣታቅማሙ። የምትሰጡት መረጃ በጥብቅ ሚስጢራዊና ያለፍቅዳችሁ የማይገለጽ ነው።

**<u>ጣልያን ኣገር ውስጥ ለብቻችሁ ያላችሁና ከዕድሜ በታችም ከሆናችሁ</u>፡**

AMARICO

- ዕድሚያችሁ ከ18 ዓመት በታች መሆኑ ሰራተኞቹን ኣስታውቋቸው፣ ምክንያቱም ከዕድሜ በታች ስለሆናችሁ ማዕከሉ ውስጥ መኖር ኣይገባችሁም። ለዕድሚያችሁ ብቃት ባለው ቦታ የመኖር መብት ኣላችሁ፣
- እናንተን ለመጠበቅ፣ እንክብካቤ የሚሰጥ ሰብ ይመደብላቹሃል። ይህ ጣልያን ኣገር ባላችሁበት ጊዜ የሚያግዛችሁ ሰው ነው (ለምሳሌ፣ ለጥገኝነት ጥያቂያችሁ የሚያስፈልጉ ሰነዶች ለማዘጋጀት በማገዝ፣ ግላዊ ቃለ መጠይቃችሁ በሚደረግበት ሰዓት በማገዝ)። ንዓኹም ንምሕላው፣ ሓልዮት ዝህብ ሰብ ክምደበልኩም እዩ። እዚ ኣብ ዓዲ ጥልያን ኣብ ዘለኹሞ ግዜ ዝሕግዘኩም ሰብ እዩ (ንምሳሌ፣ ንናይ ዑቕባ ሕቶኹም ዘድልዩ ወረቓቕቲ ንምስንዳው ብምሕጋዝ፣ ግላዊ ቃለ-መጠይቕኩም ኣብዝግበረሉ እዋን ብምሕጋዝ)። እንክብካቤ የሚያደርግላችሁ ሰው ከሌሎች ነገሮችን ጋር ጭምር የጥገኝነት ጥያቂያችሁን መግባት የማረጋገጥ ተተያቂነት ኣለው፣
- ዘመዶቻችሁን ፈልጋችሁ ማግኘት ይቻላል። የናንተና የዘመዶቻሁን ደኅንነት ለመጠበቅ ዘመዶቻችሁ የሚገኙበት ቦታ የሚመለከት መረጃ ወደ ኣገራችሁ መንግስትና ሌሎች ሰዎች የሚያስተላልፍ ሰው እንደሌለ ኣትርሱ፣
- ትምህርት የመማር መብት ኣላችሁ፣
- ዕድሚያችሁን ለማረጋገጥ፣ ይህም በናንተ ፍቃድ ሆኖ፣ ማዕከሉ ውስጥ ወይም ቅርብ በሚገኝ ሆስፒታል ልዩ ምርመራ (የእጅ ኤክስሬይ ጨረር) ወይም ሌላ ዓይነት ምርመራዎች ሊደረግላችሁ ይችላል። እነዚህ ምርመራዎች ትክክለኛው ዕድሚያችሁን በእርግጠኝነት ለማወቅ የተወሰነ ያህል ስህተት ሊኖራቸው ይችላል። የሚሰጣችሁ ዕድሜ ከትክክለኛው ዕድሚያችሁ የማይስማማ ከሆነ፣ ይህንን በሚመለከት ከሰራተኞቹ ጋር ተነጋገሩ። የሕክምና ምርመራ እንዲደረግላችሁ ኣልፈልግም ማለት ጥያቂያችሁ እንዳይታይ የሚያደርግ ወይም ውሳኔውን የሚያሰናክል ኣይደለም።

እያንዳንድ ችግርን በሚመለከት ወይም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ሰራተኛን ያነጋግሩ።

## እንደ ድፍን ኣለም ጥበቃ ጠያቂ ያላችሁ መብቶች

- የመኖሪያ ፍቃድ ከተሰጣችሁ በኃላ፣ ሃገራዊ የጤና ኣገልግሎት በመመዝገብ የጤና እገዛ የማግኘት መብት ይኖርባቹሃል።
- የስራ ጉዳይን በሚመለከት የጥገኝነት ጥያቂያችሁ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚመለከተው ኣካል በስድስት ወራት ውስጥ ውሳኔ ካልተሰጠ፣ ይህም በናንተ ጥፋት ካልሆነ፣ የመኖሪያ ፍቃዱ ለስድስት ወራት እንዲታደስና ውሳኔ የመስጠት ጉዳይ እስከሚያልቅ ድረስ እንድትሰሩ ይፈቅድላቹሃል። ቢሆንም የመኖሪያ ፍቃዱ በስራ ምክንያት ወደ መኖሪያ ፍቃድ ሊቀየር ኣይችልም።
- በተጨማሪም፣ የቤተሰባችሁን ኣባሎች ለማምጣት መጠየቅ ኣትችሉም።

## ሃገራዊ ስልጣን ያለው አካል ሊሰጣቸው የሚችል ውሳኔዎች (ሶስተኛ ደረጃ)

ስልጣን ያለው አካል በጽሑፍ መልክ፡

1. **<u>የስደተኛ ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል፡</u>**
2. **<u>የስደተኛ ፍቃድ ሳይሰጥ የሁለተኛ ደረጃ ጥበቃ ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል</u>፣** እንደዚህ የሚሆነው ወደ ኣገራችሁ ከተመለሳችሁ ሊያጠቃችሁ የሚችል ከባድ ስጋት ኣለ ብሎ ሲያስብ ነው፡
3. **<u>የስደተኛ ፍቃድ ላይሰጥ ይችላል</u>፣** ቢሆንም ከባድ የሰብኣዊ ሁኔታዎች ኣሉ ብሎ በማመን ለፖሊስ ኣካል **<u>በሰብኣዊ ሁኔታዎች ምክንያት የመኖሪያ</u>** ፍቃድ እንዲሰጣችሁ ሊጠይቅ ይችላል፡
4. **<u>የስደተኛ ፍቃድ ባለመስጠት ጥያቄያችሁን ላይቀበለው ይችላል</u>።**
5. **ጥያቄያችሁ መሰረታዊ ብቃት ከሌለው ላይቀበለው ይችላል፣** ይህም የድፍን ኣለም ጥበቃ የሚያስፈልግበት ምክንያትን የሚገልጹ ማስረጃዎች ከሌሉ ነው፣ ወይም ጥያቄውን ያቀረባችሁት ምክንያት እንዳትባረሩ ወይም ሳይቀበላችሁ እንዳይቀር ብላችሁ ያደረጋችሁት ነገር ከሆነ። እንዲህ በሆነበት ሰዓት ስልጣን ያለው ኣካል የሰጠውን ውሳኔ በሚመለከት የምታቀርቡት ተቃውሞ ጉዳዩን ሊያቆመው ኣይችልም። ቢሆንም ከባድና መሰረት ያላቸው ነጥቦች ቢኖሩ ቀኑ እንዲቀየርላችሁ ፍርድ ቤትን መጠየቅ ትችላላችሁ፣ ፍርድ ቤቱ በሚቀጥሉት ኣምስት ቀናት ውስጥ ይወስናል።

## የስደተኛ ፍቃድ ከተሰጣችሁ

ስልጣን ያለው ኣካል የጥገኝነት መኖሪያ ፍቃዳችሁን በፖሊስ እንዲሰጣችሁ ስራ ይጀምራል።

የጥገኝነት መኖሪያ ፍቃዱ ለ5 ዓመታት የሚያገለግል ሆኖ ቀኑ ሲያልቅ ማሳደስ ይቻላል።

### የስደተኛ መብቶች፡

- ስራ የማግኘት ዕድል፣
- የቤተሰብ ኣባሎች የማምጣት መብት
- ማሕበራዊ እገዛ የማግኘት መብት
- የጉዞ ሰነድ የምታገኙበት መብት

የጉዞ ሰነድ ማመልከቻ የሚከተሉት ሰነዶችን ኣዘጋጅተው ወደ ፖሊስ ቢሮ ያቅርቡዋቸው፡
  - የጉዞ ሰነድ ማመልከቻ የሚሞላ ፎርም
  - 2 የፓስፖርት ፎቶ
  - 1 ቴምብር
  - ለፓስፖርት የሚሆን ቴምብር
  - ቀኑ ያላለፈ የመኖሪያ ፍቃድ ቅጂ
- የህዝብ ትምህርት የማግኘት መብት፣
- የተባበሩት የኣውሮጳ ኣገሮች ውስጥ (ከዴንማርክና እንግሊዝ ኣገር በተለይ) ያለ ፍቃድ ከሶስት ወራት በላይ ለማይሆን ጊዜ በነጻ የመንቀሳቀስ መብት፣
- ጣልያን ኣገር ውስጥ ለ5 ዓመታት ከቆያችሁ በኃላ የጣልያን ኣገር ዜግነት የመጠየቅ መብት፣
- የማግባት መብት (ፍቃዱ የሚሰጠው በ ዩ ኤን ኤች ሲ ኣር (UNHCR) ነው)፣
- የመንግስት መኖሪያ ቤት ሊያሰጣችሁ የሚያስችል መብት፣
- የመንጃ ፍቃድ እንድታገኙ የሚያስችል መብት።

ተጨማሪ መረጃና እገዛ ለማግኘት፣ ባላችሁበት ቦታ የስደተኞችና ጥገኝነት ጥያቄ ኣቅራቢዎች የጥበቃ ጉዳዮች ከሚያካሂዱ ድርጅቶች ጋር ተገናኙ።

## የሁለተኛ ደረጃ ጥበቃ ፍቃድ ከተሰጣችሁ

ስልጣን ያለው አካል የሰጠው ውሳኔ ይነገራቹሃል፣ የሁለተኛ ደረጃ ጥበቃ ፍቃዳችሁን ከፖሊስ ቢሮ ትወስዳላችሁ።

የሁለተኛ ደረጃ ጥበቃ መኖሪያ ፍቃድ ለሶስት ዓመታት የሚያገለግል ሲሆን ቀኑ ሲያልቅ ማሳደስ ይቻላል። ይህም ሃገራዊ ስልጣን ያለው አካል ጉዳያችሁን ድጋሚ ካየው በኃላ ሆኖ አንዳንዴ አዲስ ስብሰባ ሳያደርግ ይሆናል።

በተጨማሪ የሁለተኛ ደረጃ ጥበቃ ፍቃድ በስራ ምክንያት ወደ መኖሪያ ፍቃድ መቀየር ይቻላል። ይህም መታወቂያ፣ ፓስፖርት ወይም የጉዞ ሰነድ ያላችሁ ከሆነ ነው (እንዴት እንደዛ ለማድረግ እንደምትችሉ ለማወቅ የስደተኞችን መብቶች ለመጠበቅ የሚሰሩ ድርጅቶችን ይጠይቁ **<u>ይህም የመኖሪያ ፍቃዳችሁ ቀኑ ሳያልቅ መሆን አለበት</u>**)፡

**የሁለተኛ ደረጃ ጥበቃ መኖሪያ ፍቃድ ለተሰጣቸው ያልዋቸው መብቶች፡**

- የስራ ዕድል (ይህ ከተሰጣችሁ ፍቃድ ለማይረዝም ጊዜ ነው)፣
- የጤና እገዛ የማግኘት መብት፣
- የቤተሰብ አባሎችን የማምጣት መብት፣
- ማሕበራዊና የጽዳት እገዛ የማግኘት መብት፣
- ለውጭ አገር ዜጎች የጉዞ ሰነድ መስጠት፣ ይህም ፓስፖርት ከሌላችሁ ነው፣
- የመንግስት መኖሪታ ቤት ሊያሰጣችሁ የሚያስችል መብት፣

ተጨማሪ መረጃና እገዛ ለማግኘት፣ ባላችሁበት ቦታ የስደተኞችና ጥገኝነት ጥያቄ አቅራቢዎች የጥበቃ ጉዳዮች ከሚያካሂዱ ድርጅቶች ጋር ተገናኙ።

## በሰብአዊ ሁኔታዎች ምክንያት የመኖሪያ ፍቃድ ከተሰጣችሁ

ስልጣን ያለው አካል የሰጠው ውሳኔ ይነገራቹሃል፣ በሰብአዊ ሁኔታዎች ምክንያት የተሰጠው ፍቃዳችሁን ከፖሊስ ቢሮ ትወስዳላችሁ።

በሰብአዊ ሁኔታዎች ምክንያት የተሰጠው መኖሪያ ፍቃድ ለ፤ ዓመት የሚያገለግል ሲሆን ፓስፖርት ካላችሁ ለስራና እንደ መኖሪያ ፍቃድ ወደሚያገለግል ፍቃድ መቀየር ይቻላል።

**በሰብአዊ ሁኔታዎች ምክንያት መኖሪያ ፍቃድ ለተሰጣቸው ሰዎች ያላቸው መብቶች፡**

- ጣልያን አገር ውስጥ መስራት ትችላላችሁ፣
- የጤና እገዛ ለማግኘት ትችላላችሁ፣
- ለውጭ አገር ዜጎች የሚሆን የጉዞ ሰነድ እንዲሰጣችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ፣ ይህም ፓስፖርት ከሌላችሁ ነው።

ተጨማሪ መረጃና እገዛ ለማግኘት፣ ባላችሁበት ቦታ የስደተኞችና ጥገኝነት ጥያቄ አቅራቢዎች የጥበቃ ጉዳዮች ከሚያካሂዱ ድርጅቶች ጋር ተገናኙ።

**ይግባኝ ማለት (አራተኛ ደረጃ)**

**ሃገራዊ ስልጣን ያለው አካል የሰጠው ውሳኔ ከሰማችሁበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ፍርድ ቤት ዘንድ ይግባኝ ማለት ትችላላችሁ።**

ለጥገኝነት ጠያቂዎች በሚሆን የመንግስት ማዕከል (Cara) ወይም *(Centro Identificazione ed Espulsione)* - ማንነትን የመመርመርና ማስወጫ ማዕከል (CIE) ውስጥ ካላችሁ፣ ውሳኔ ከተሰጣችሁ ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ፍርድ ቤት ዘንድ ይግባኝ የማለት መብት ኣላችሁ (30 ኣይደለም)።

**የይግባኝ ጥያቄ ስልጣን ያለው አካል ለሰጠው ውሳኔ በጊዜያዊ መልክ ሊያቆመው የሚችልበት ሁኔታዎች:**

ሃ) ጥያቂያችሁ ባቀረባችሁበት ጊዜ የመኖሪያ ፍቃድ ከነበራችሁ፣
ለ) ማንነታችሁን ወይም ዜግነታችሁን ለማወቅ የመንግስት ማስተናገጃ (CARA) ውስጥ ከነበራችሁ፣

ይህ ጣልያን ኣገር ውስጥ በሶስት ወራት ውስጥ ጥገኝነት ለመጠየቅ መኖሪያ ፍቃድ ተቀብላችሁና በሕጋዊ ሁኔታ የመቆየት መብት እያላችሁ የፍርድ ቤት ውሳኔ እየጠበቃችሁ እያላችሁ ሲሆን ነው።

**ኣትኩረው ይመልከቱ**

**ተከትለው በሚገኙት ምሳሌዎች የይግባኝ ጥያቄ ማቅረብ በመቀጠል ላይ የሚገኝን ክርክር ሊያቆመው ኣይችልም:**

- ስልጣን ያለው ኣካል ጉዳያችሁን ኣይቶ ተቀባይነት እንደሌለው ካሳወቀ፣
- ስልጣን ያለው ኣካል ጉዳያችሁን ኣይቶ የሁለተኛ ደረጃ ጥበቃ ፍቃድ ከፈቀደላችሁ፣
- ስልጣን ያለው ኣካል የሰጠው ውሳኔ ከመንግስት ማዕከል (CARA) ያለፍቃድ ከወጣችሁ በኃላ ከሆነ፣
- ጥያቄያችሁ ብግልጽ መሰረት ስለሌለው የእምቢተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ፣
- የይግባኝ ጥያቄ ያቀረባችሁት ከጥበቃ ስታመልጡ ወይም ወይም ለማምለጥ እየሞከራችሁ ወይም ከዛ በኃላ ተይዛችሁ ወደ መንግስት ማዕከል (CARA) ከገባችሁ በኃላ ወይም ያለፍቃድ እየኖራችሁ ተይዛችሁ እንደሆነ ነው፤
- ሲ ኣይ ኢ (CIE) ውስጥ ተይዛችሁ ካላችሁ።

ይህም ዝርዝር ውስጥ ካሉት ምሳሌዎች፣ የሁለተኛ ደረጃ ጥበቃ ፍቃድ የተፈቀደላቸውን በስተቀር፣ ጣልያን ኣገር ውስጥ የመቆየት መብት ሳይኖራችሁ ወደ ኣገራችሁ ለመመለስ የምትችሉትን፣ ቢሆንም ከባድና መሰረት ያላቸው ነጥቦች ካሉ ፍርድ ቤት ዘንድ ቀኑ እንዲቀየርላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ።

በሕግ መሰረት የጠበቃ እገዛ መጠየቅ ኣለባችሁ። ጠበቃውን መክፈል የማትችሉ ከሆናችሁ፣ ነጻ የሆነ (በመንግስት የሚከፈል) የሕግ እገዛ እንዲሰጣችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ።

ተጨማሪ መረጃና እገዛ ለማግኘት፣ ባላችሁበት ቦታ የስደተኞችና ጥገኝነት ጥያቄ ኣቅራቢዎች የጥበቃ ጉዳዮች ከሚያካሂዱ ድርጅቶች ጋር ተገናኙ።

**ኣትኩረው ይመልከቱ:**
**የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ፍትሃዊ ሆኖ ካልተሰማችሁ፣** ወደ ይግባኝ ፍርድ ቤት በመቅረብ ከባድና መሰረት ያላቸውን ነጥቦች ሲኖሩ ጣልያን ኣገር ውስጥ ለመቆየት መጠየቅ ትችላላችሁ።

**የይግባኝ ፍርድ ቤት የሚሰጠውን ውሳኔ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዘንድ ይግባኝ ማለት ትችላላችሁ።**

**ኣትኩረው ይመልከቱ:** የይግባኝ ጥያቄ ከመታየቱ በፊት ያቀረባችሁት መረጃ በደንብ ያልታየ ሆኖ ከተሰማችሁ፣ ጉዳያችሁን መጀመሪያ ካየው ስልጣን ያለው ኣካል ዘንድ ድጋሚ እንዲታይላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ። ይህ ስራ የይግባኝ ጉዳዩን ኣያቋርጠውም።

የይግባኝ ጉዳዩን በሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ባላችሁበት ቦታ የሚገኙና የስደተኞችን የጥበቃ ጉዳዮች ከሚያካሂዱ ድርጅቶች ወይም ባላችሁበት ማሕበረሰብ የሚገኝ የውጭ ኣገር ዜጎች ሕግ ቢሮ ወይም ከጠበቃ ጋር ይገናኙ።

**የድፍን ኣለም ጥበቃ ፍቃዳችሁ ሲቋረጥ ወይም ሲሰረዝ**

## 1) የስደተኞች ፍቓድ

የተሰጣችሁ የስደተኞች ፍቃድ ሊቋረጥ የሚችልበት ሁኔታዎች፡

ሃ) በፍቃዳችሁ የኣገራችሁ ጥበቃ ድጋሚ ከተቀበላችሁ (ለምሳሌ ከተመለሳችሁ ወይም ወደ ያገራችሁ ኤምባሲ በመሄድ ፓስፖርት እንዲሰጣችሁ ከጠየቃችሁ ወይም ከተሰጣችሁ፣ ወዘተ)፣

ለ) ተከልክላችሁ የነበረውን ያገራችሁ ዜግነት ፍቃደኛ ሆናችሁ ከተቀበላችሁ፣

ሓ) የጣልያን ኣገር ወይም ሌላ ዜግነት የተቀበላችሁ ሆኖ ከተቀባላቹባት ኣገር ጥበቃ ይደረግላችሁ እንደሆነ፣

መ) በፍቃዳችሁ ህይወታችሁን ድጋሚ ኣገራችሁ ውስጥ ከመሰረታችሁ፣

ሠ) የስደተኛ ፍቃድ እንዲሰጣችሁ ያደረጉት ምክንያቶች በመቀየራቸው ያገራችሁን ጥበቃ ለማግኘት ወደ ኣገራችሁ በሰላም መመለስ የምትችሉ ከሆናችሁ፣

ረ) ኣገር የሌላቸው ሰዎች ሆናችሁ ትኖሩበት ወደነበር ኣገር ለመመለስ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ፣ ይህም የስደተኛ ፍቃድ እንዲሰጣችሁ ያደረጉት ምክንያቶች ከተቀየሩ ይሆናል፣

ሠ)ና ረ) ላይ ያሉት ምሳሌዎች ተግባር ላይ እንዲውሉ የሁኔታው ለውጥ ጊዜያዊ መሆን የለበትም፣ እንደዛውም የውከባ ስጋታችሁ በሙሉ የሚያስወግዱ መሆን ኣለባቸው።

በተጨማሪ ወደ ኣገራችሁ መመለስ የማያስችሉ ሌሎች ሰብኣዊ ምክንያቶች መኖር የለባቸውም።

የስደተኛ ፍቃድ መቋረጥ በግላዊ ሁኔታችሁ ምርመራ፣ ሃገራዊ ስልጣን ባለው ኣካል የጥገኝነት መብት ነው የሚሰጠው።

ሃገራዊ ስልጣን ያለው ኣካል የመቋረጥ ስራ መጀመሩና፣ የሚደረግበት ምክንያትን በጽሑፍ ያሳውቃቹሃል። ይህ እናንተ ማንኛውም ዓይነት ለጉዳዩ ኣስፈላጊ ናቸው የምትሉዋቸውን ነገሮች በጽሑፍ ለማቅረብ የሚሰጣችሁ ዕድል ነው። ከዚህ ቀጥሎ ወደ ግላዊ ቃለ መጠይቃችሁ መጥታችሁ እንድታብራሩ ትጠራላችሁ።

የስደተኛ ፍቃዳችሁ ሊሰረዝበት የሚችሉ ምክንያቶች፣ የቀረበው በተሰጡት ትክክለኛ ያልሆኑ ማስረጃዎች ተመስርቶ ከሆነ ወይም በፍቃዳችሁ ያልተገለጹ ሌሎች መረጃዎች/ወይም ሁኔታዎች ሲኖሩ ወይም የተመሰረተበት ሰነዶች ትክክለኛ ሳይሆኑ ሲገኙ ነው።

ፍቃዱ በተጨማሪ ከተሰጠ ባኃላ ሊሰረዝበት የሚችል ሁኔታዎች፣ ፍቃዱ እንዳይሰጥ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሲገኙ፣ በተለይም፣

ሃ) በጀኒቫ ስብሰባ የተሰጠ ብቃት እንደሌላችሁ የሚያደርግ ምክንያት ሲኖር (ጸረ ሰብኣዊና፣ ጸረ ሰላም የሆነ ወንጀል ፈጽማችሁ ከሆነ፣ በጦርነት ወቅት የሚደረግ ወንጀል ፈጽማችሁ ከሆነ ወይም በተባበሩት መንግስታት ኣንድ ኣካል ከ ዩ ኤን ኤች ሲ ኣር (U.N.H.C.R.) በስተቀር ጥበቃ ወይም እገዛ እንደሚሰጣችሁ ከታወቀ)

ለ) ለጣልያን ኣገር ደህንነት ኣስጊ መሆናችሁ የሚያሳዩ ነጥቦች ሲኖሩ፣

ሓ) ለህዝባዊ ደህንነት ኣስጊ መሆናችሁ የሚያረጋግጥ ሁኔታ ሲኖር፣ በጽሑፍ 407፣ ዓንቀጽ 2፣ ዝርዝር ሃ) (Art. 407, paragraph 2, item a)) የወንጀለኞጅ ኣቀራረብ እንደሚለው ወንጀለኛ መሆናችሁ የሚገልጽ ፍርድ ከተሰጠ።

የስደተኛ ፍቃድ መሰረዝ በግላዊ ሁኔታችሁ ምርመራ፣ ሃገራዊ ስልጣን ባለው ኣካል የጥገኝነት መብት ነው የሚሰጠው።

ሃገራዊ ስልጣን ያለው ኣካል የመሰረዝ ስራ መጀመሩና፣ የሚደረግበት ምክንያትን በጽሑፍ ያሳውቃቹሃል። ይህ እናንተ ማንኛውም ዓይነት ለጉዳዩ ኣስፈላጊ ናቸው የምትሉዋቸውን ነገሮች በጽሑፍ ለማቅረብ የሚሰጣችሁ ዕድል ነው። ከዚህ ቀጥሎ ወደ ግላዊ ቃለ መጠይቃችሁ መጥታችሁ እንድታብራሩ ትጠራላችሁ።

## 2) የሁለተኛ ደረጃ ጥበቃ ፍቃድ

የተሰጣችሁ የሁለተኛ ደረጃ ጥበቃ ፍቃድ እንዲፈቀድላችሁ ያስቻሉ ሁኔታዎች ሲቆሙና ወይም ሲቀየሩ፡ ጥበቃውም ኣስፈላጊ ሳይሆን ሲገኝ ሊቋረጥ ይችላል። ይህም የሁኔታዎች ለውጥ ታላቅና ጊዜያዊ ያልሆነ ሆኖ ሲገኝ፣ ወደ ኣገራችሁ ከተመለሳችሁ *"ከባድ ስጋት"* የማይደርስባችሁና ሌሎች መመለስ የማያስችሉ ከባድ የሰብኣዊ ሁኔታዎች የሌሉበት መሆን ኣለበት።

የሁለተኛ ደረጃ ፍቃድ መቋረጥ በግላዊ ሁኔታችሁ ምርመራና የተሰጠበት *"ከባድ ስጋት"* ምክንያት፣ ሃገራዊ ስልጣን ባለው ኣካል የጥገኝነት መብት ነው የሚሰጠው።

ሃገራዊ ስልጣን ያለው ኣካል የመቋረጥ ስራ መጀመሩና፣ የሚደረግበት ምክንያትን በጽሑፍ ያሳውቃቹሃል። ይህ እናንተ ማንኛውም ዓይነት ለጉዳዩ ኣስፈላጊ ናቸው የምትሉዋቸውን ነገሮች በጽሑፍ ለማቅረብ የሚሰጣችሁ ዕድል ነው። ከዚህ ቀጥሎ ወደ ግላዊ ቃለ መጠይቃችሁ መጥታችሁ እንድታብራሩ ትጠራላችሁ።

የሁለተኛ ደረጃ ፍቃዳችሁ ሊሰረዝበት የሚችሉ ምክንያቶች፣ የቀረበው በተሰጡት ትክክለኛ ያልሆኑ ማስረጃዎች ተመስርቶ ከሆነ ወይም በፍቃዳችሁ ያልተገለጹ ሌሎች መረጃዎች/ወይም ሁኔታዎች ሲኖሩ ወይም የተመሰረተበት ሰነዶች ትክክለኛ ሳይሆኑ ሲገኙ ነው።

ፍቃዱ በተጨማሪ ከተሰጠ ባኃላ ሊሰረዝበት የሚችል ሁኔታዎች፣ ፍቃዱ እንዳይሰጥ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሲገኙ፣ በተለይም፣

ሃ) በጀኒቫ ስብሰባ የተሰጠ ብቃት እንደሌላችሁ የሚያደርግ ምክንያት ሲኖር (ጸረ ሰብኣዊና፣ ጸረ ሰላም የሆነ ወንጀል ፈጽማችሁ ከሆነ፣ በጦርነት ወቅት የሚደረግ ወንጀል ፈጽማችሁ ከሆነ ወይም በተባበሩት መንግስታት ኣንድ ኣካል ከ ዩ ኤን ኤች ሲ ኣር (U.N.H.C.R.) በስተቀር ጥበቃ ወይም እገዛ እንደሚሰጣችሁ ከታወቀ)፡

ለ) ጣልያን ኣገር ውስጥ ወይም ከዛ ውጭ የፈጸማችሁት ወይም ያስጀመራችሁት ከባድ ወንጀል ሲኖር። የወንጀሉ ክብደት የሚታየው በቅጣቱ መጠን ሆኖ በጣልያን ኣገር ሕግ መሰረት ከኣራት ዓመታት የማያንስና የላቀውም የኣስር ዓመታት ነው፡

የሁለተኛ ደረጃ ፍቃድ መሰረዝ በግላዊ ሁኔታችሁ ምርመራና፣ ሃገራዊ ስልጣን ባለው አካል የጥገኝነት መብት ነው የሚሰጠው። ሃገራዊ ስልጣን ያለው አካል የመሰረዝ ስራ መጀመሩና፣ የሚደረግበት ምክንያትን በጽሑፍ ያሳውቃቹሃል። ይህ እናንተ ማንኛውም ዓይነት ለጉዳዩ አስፈላጊ ናቸው የምትሉዋቸውን ነገሮች በጽሑፍ ለማቅረብ የሚሰጣችሁ ዕድል ነው። ከዚህ ቀጥሎ ወደ ግላዊ ቃለ መጠይቃችሁ መጥታችሁ እንድታብራሩ ትጠራላችሁ።

## ወደ አገራችሁ በፍላጎት መመለስ

ወደ አገራችሁ በደህንነትና በክብር መመለስ መብታችሁ ነው።

የድፍን አለም ጥበቃ ጥያቄ አቅራቢ ከሆናችሁ፣ **ፍቃድ ያልተሰጣችሁ ሆኖ ይህም ከተነገራችሁ ጀምሮ 30 ቀናት ያላለፉ ከሆነ**፣ የስደተኛች ፍቃድ ከነበራችሁ፣ የሁለተኛ ደረጃ ፍቃድ ከነበራችሁ ወይም በሰብኣዊ ምክንያቶች ፍቃድ ያላችሁ ከሆናችሁ ወደ አገራችሁ በፍላጎት መመለስ ትችላላችሁ።

እገዛ ያለው በፍላጎት የመመለስ ኣሰራር የሚያቀርባቸው ነገሮች፡ ምክር የመስጠት ኣገልግሎት፣ ኣገራችሁን በሚመለከት ኣዳዲስ መረጃዎች መስጠት፣ ከኤምባሲ የሚገኝ የጉዞ ሰነድ ለማውጣት እገዛ ማድረግ፣ ለጉዞ ማዘጋጀት፣ መጨረሻ እስከምትሄዱበት ያለው የጉዞ ክፍያ መሸፈንና ወደ ማሕበረሰቡ ተመልሶ ለመግባት የሚያስችል ገንዘብ መስጠት።

በፍላጎት ወደ አገራችሁ የመመለስ እቅድ ለመባረር ዝግጅት ላይ ያላችሁ ከሆናችሁ ልትጠቀሙበት እንደማትችሉ ኣትርሱ።

ወደ አገራችሁ በፍላጎት ለመመለስ የሚያስችል መረጃና እገዛ ማግኘት መብታችሁ ነው። ተከትለው ከተጠቀሱ ጋር መገናኘት ትችላላችሁ፡

- የማዕከል ሰራተኞች።

### **የቃላት ትርጉም ዝርዝር**

**የውስጥ ጉዳዮች ሚኒስቴር፡** ቀንደኛ ተጠያቂነቱ ስደትና ጥገኝነት የሆነ የመንግስት አስተዳደር ማእከላዊ አካል ነው።

**አስተዳዳሪ፡** ማእከላዊ ያልሆነ የውስጥ ጉዳዮች ሚኒስቴር ክልላዊ አካል ሆኖ የመንግስትም ክልላዊ ቢሮ ነው።

**የፖሊስ ክፍል፡** አስተዳዳሪ አካል ሲሆን በማንኛውም ክልል ያለ የፖሊስ እንቅስቃሴ የሚመራና የሚያካሂድ ነው። በማንኛውም የፖሊስ ክፍል አንድ የመጤዎችና ጥገኞች ጉዳይ የሚያካሂድ ቢሮ ይኖራል (ለምሳሌ የጥገኝነት ጥያቄ ሊቀርብለት ይችላል፣ የመኖሪያ ፍቃድና የጉዞ ሰነዶችን ያሳድሳል)።

**የጥገኝነት መብቶች ሃገራዊ ስልጣን ያለው አካል፡** ሃገራዊ ስልጣን ያለው አካልን መምራትና ማካሄድ፣ ለአካሉ አባሎች አዳዲስ መረጃዎች መስጠትና አሃዛዊ መረጃ ማከማቸትን የመሳሰሉ ተግባሮች ይኖሩታል። የተሰጡ ፍቃዶችን የመሰረዝና ማቋረጥ ውሳኔዎችን የመስጠት ስልጣን አለው።

**የድፍን አለም ጥበቃ ሃገራዊ ስልጣን ያለው አካል፡** የድፍን አለም ጥበቃ ፍቃድ ጥያቄ የማየት ተጠያቂነት አላቸው። እነዚህ ከአስር የማይበዙ ሲሆኑ፣ ከዚህ ቀጥለው በዝርዝር ይገኛሉ፡

1. ጎሪዚያ (GORIZIA)፡ ፍሪዩሊ-ቨነዚያ፣ ጂዩሊያ፣ ቨነቶ፣ ትረንቲኖ፣ አልቶ አዲጀ (Friuli-Venezia Giulia, Veneto, Trentino Alto Adige) ክልሎች ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች የማየት ስልጣን ያለው፣
2. ሚላን (Milan)፡ ሎምባርዲ (Lombardy) ክልል ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች የማየት ስልጣን ያለው፣
3. ሮም (ROME)፡ ላዚዮ፣ አብሩዞ፣ ሳርደኛ፣ ቶስካና፣ ማርቼ፣ ኡምብሪያ (Lazio, Abruzzo, Sardegna, Toscana, Marche, Umbria) ክልሎች ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች የማየት ስልጣን ያለው፣
4. ፎጂያ (FOGGIA)፡ ፎጂያና ባርለታ-አንድሪያ-ትራኒ (Foggia and Barletta-Andria-Trani) ክልሎች ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች የማየት ስልጣን ያለው፣
5. ሲራኩሳ (SIRACUSA)፡ ሲራኩሳ፣ ራጉሳ፣ ካልታኒሰታ፣ ካታኒያ (Siracusa, Ragusa, Caltanissetta, Catania) ክልሎች ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች የማየት ስልጣን ያለው፣
6. ክሮቶነ (CROTONE)፡ ካላብሪያና ባሲሊካታ (Calabria and Basilicata) ክልሎች ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች የማየት ስልጣን ያለው፣
7. ትራፓኒ (TRAPANI)፡ አግሪጀንቶ፣ ትራፓኒ፣ ፓለርሞ፣ መሲና፣ ኤና (Agrigento, Trapani, Palermo, Messina, Enna) ክልሎች ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች የማየት ስልጣን ያለው፣
8. ባሪ (BARI)፡ ባሪ፣ ብሪንድሲ፣ ለቸና ታራንቶ (Bari, Brindisi, Lecce and Taranto) ክልሎች ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች የማየት ስልጣን ያለው፣
9. ካሰርታ (CASERTA)፡ ካምፓኒያና ሞሊሰ (Campania and Molise) ክልሎች ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች የማየት ስልጣን ያለው፣
10. ቲዩሪን (TURIN)፡ ቫለ ድአኦስታ፣ ፒየሞንተ፣ ሊጉሪያ፣ ኤሚሊያ ሮማኛ (Valle d'Aosta, Piemonte, Liguria, Emilia Romagna) ክልሎች ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች የማየት ስልጣን ያለው።

**የጥገኝነት ጥያቄ አቅራቢዎች መስተንግዶ ማዕከል (ካራ (CARA))፡** የድፍን አለም ጥበቃ ጥያቄ አቅርበው ጉዳያቸው በሚታይበት ጊዜ የሚቆዩበት ማዕከል ነው። እዛ የሚቆዩባቸው ምክንያቶች፡
ጥያቄ አቅራቢዎቹ የጥገኝነት ጥያቄ አቅራቢዎች መስተንግዶ ማዕከል (ካራ (CARA)) ውስጥ የሚኖሩባቸው ምሳሌዎች፡
ሃ) ዜግነታቸው ወይም ማንነታቸውን ለማወቅ አስፈላጊ ሲሆን፣ የጉዞ ሰነድ ወይም መታወቂያ ከሌላቸው፣ ወይም አገር ውስጥ እንደገቡ ሕጋዊ ያልሆነ ሰነድ ያቀረቡ ከሆኑ፣
ለ) ከድንበር ጠባቂዎች ከማምለጣችሁ በኃላ ወይም ለማምለጥ እየሞከራችሁ ተይዛችሁ ወይ ከዛ ቀጥላችሁ ጥያቄ ያቀረባችሁ ከሆናችሁ፣
ሐ) ያለፍቃድ እየኖራችሁ እያለ ተይዛችሁ ከዛ በኃላ ጥያቄ ስታቀርቡ።
ምሳሌ ሃ)ን በሚመለከት ጥያቄ አቅራቢው ማዕከሉ ውስጥ የሚቆይበት ከሃያ ቀናት ለማይረዝም ጊዜ ነው። ሌሎች ምሳሌዎችን በሚመለከት ማንኛውም ጥያቄ አቅራቢ ማዕከሉ ውስጥ የሚቆይበት ሃገራዊ ስልጣን ባለው አካል ጥያቄውን ምርመራ እንዲካሄድለት ለሚያስፈልግ ጊዜ ያህል ብቻ ሆኖ ማንኛውም ጉዳይ ከሳላሳ አምስት ቀናት ለማይረዝም ጊዜ ነው።

**የስደተኞች ጥበቃ ማኅበሮች፡** የስደተኞች የሕግና ጥበቃ ማስተዳደር ተጠያቂነት ያላቸው ማኅበሮች። ከነዚህ ማኅበሮች ጋር ለመገናኘት፣ አስፈላጊ አድራሻዎችን የያዘውን ገጽ ይመልከቱ ወይም እባክዎን ማዕከሉ ውስጥ ካለ ሰራተኛ ጋር ይገናኙ።

**የጥገኝነት ጠያቂዎችና ስደተኞች ጥበቃ መዋቅር** (ስፕራር (SPRAR))፡ ስፕራር የመስተንግዶና ማሕበረሰብ ውስጥ የመቀላቀል መዋቅር ነው፣ የሚካሄደው በውስጥ ጉዳዮች ሚኒስቴርና የክልል አካሎች ሲሆን፣ አገር ውስጥ በመጀመሪያ የሚደረግ ለጥገኝነት ጠያቂዎችንና

AMARICO

**የማዕከል ሰራተኞች፡** እነዚህ የመስተንግዶ ማዕከል (ካራ (CARA)) ውስጥ የሚገኙ ሰራተኞች ሲሆኑ የድፍን አለም ጥበቃ ጠያቂዎችን ለመንከባከብ የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት፣ ስነ ልቦናዊና ሕጋዊ ችግሮችን ለመፍታት የማስተዳደርና/ማካሄድ ተጠያቂነት ያላቸው ናቸው።

**የቋንቋና ባህል ሽማግሌዎች፡** ማዕከል ውስጥ በሚገኙ የድፍን አለም ጥበቃ ጠያቂዎችና በማዕከል ሰራተኞች/ወይም ሃገራዊ ስልጣን ያለው አካል አባሎች መሃል ለመግባባት የሚያግዙ፣ እንደዛውም ባህላዊና የባህርይ ልዩነቶችን የሚያስተረጉሙ ናቸው።

**የመኖሪያ ፍቃድ፡** ጣልያን አገር ውስጥ በሕጋዊ መልክ ለምኖር ፍቃድ የሚሰጥ ሰነድ ነው።

**የጉዞ ሰነድ፡** የስደተኞች ፍቃድ ካላችሁ ከጣልያን አገር ውጭ ለመጓዝ የሚፈቅድላችሁ ሰነድ ነው።

**የጉዞ ፍቃድ፡** በሁለተኛ ደረጃ ጥበቃ ምክንያት ወይም ሰብአዊ ጥበቃ የመኖሪያ ፍቃድ ከተሰጣችሁ ከጣልያን አገር ውጭ ለመጓዝ የሚፈቅድላችሁ ሰነድ ነው።

***መግለጫ ሕግጋት፡***

- **የድፍን አለም፡**
  ጀኒቫ ስብሰባ 1951 የስደተኞች ፍቃድን የሚመለከት

  - የተባበሩት የአውሮጳ አገሮች፡
    ሕግ ቁጥር 343/2003 የሚገልጸው አንድ የሌላ አገር ዜጋ አንዲት አባል አገር ውስጥ የሚደረግለት የምርመራና የጥገኝነት ጥያቄን የመቀበል ብቃት ነው።

- ***ሃገራዊ***
  - ሕጋዊ ድንጋጌ 30/12/1989፣ ቁጥር 416 (የፖለቲካዊ ጥገኝነት ጉዳይ፣ ጣልያን አገር ውስጥ ያሉ ተጨማሪ ማሕበረሰብ ዜጎችና አገር የሌላቸው ሰዎች የመግባትና የመኖር አስቸኳይ ሕግጋት) የተቀየረው፣ ለውጥ የተደረገው ከሕግ 28/02/1990፣ ቁጥር 39 ተቀይሮ የነበርው ከሕግ ቁጥር 189/2002፣
  - የሪፑብሊክ ፕረዚደንት ድንጋጌ 16/09/2004፣ ቁጥር 303፣ የስደተኞች ፍቃድ የሚሰጥበት አሰራር በሚመለከት፣
  - ሕጋዊ ድንጋጌ 30/05/2005፣ ቁጥር 140፣ ጥቅም ላይ የዋለበት መምሪያ 2003\9\CE የሚገልጸው ኣባል ኣገሮች የጥገኝነት ጥያቄ ለሚያቀርቡ የሚደርግላቸው መስተንግዶ በሚመለከት ቢያንስ መኖር ያለባቸው ሕግጋት ነው፣
  - ሕጋዊ ድንጋጌ 25/07/1998፣ ቁጥር 286 የስደተኞች ግላዊ ጽሑፍ።
  - ሕጋዊ ድንጋጌ 28/01/2008፣ ቁጥር 25ና ሕጋዊ ድንጋጌ 03/10/2008፣ ቁጥር 159 ጥቅም ላይ የዋለበት መምሪያ 2005\85\CE የምክር ቤት 01/12 ኣባል ኣገሮች ውስጥ የስደተኞች ፍቃድ የመስጠትና መሰረዝ በሚመለከት ቢያንስ መኖር ያለባቸው ሕግጋት ነው፣
  - ሕጋዊ ድንጋጌ 19/11/2007፣ ቁጥር 251 ጥቅም ላይ የዋለበት መምሪያ 2004\83\CE የምክር ቤት 29/04/2004 ኣባል ኣገሮች ለሶስተኛ ኣገር ዜጎች ወይም ኣገር የሌላቸው ሰዎች ወይም የአለም ድፍን ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የስደተኞች ፍቃድ መስጠት በሚመለከት ቢያንስ መኖር ያለባቸው ሕግጋት ነው፣ እንደዛውም የተሰጠውን ጥበቃ በሚመለከት ቢያንስ መኖር ያለባቸው ሕግጋት ነው፣

AMARICO

**አስፈላጊ የመገናኛ መረጃ**

**የውስጥ ጉዳዮች ሚኒስቴር፡ www.interno.it**
ተዛማጅ የጥገኝነት ክፍል በሚመለከት ዜና፣ ጥያቄ የማቅረብና የጥበቃ ፍቃድ መስጠትን የሚመለከት መረጃ የሚሰጥ የውስጥ ጉዳዮች ሚኒስቴር ወብ ሳይት ነው።

**የሃገር ፖሊስ፡ www.poliziadistato.it**
ሃገራዊ ፖሊስ ቢሮ፣ ክፍሎችና፣ የዜጎች አገልግሎት የት እንደሚገኙ መረጃ የሚሰጥ የሃገር ፖሊስ ወብ ሳይት ነው።

**ማእከላዊ አገልግሎት፡ www.serviziocentrale.it**
በውስጥ ጉዳዮች ሚኒስቴርና በአካባቢያዊ አካሎች የሚካሄድ ሃገራዊ መስተንግዶና ወደ ማሕበረሰብ የመቀላቀል ስራ (SPRAR) በሚመለከት አስፈላጊ መረጃ ልታገኙ የምትችሉበት ወብ ሳይት ነው።

- **ድፍን ኣለም**

**ዩ ኤን ኤች ሲ ኣር (UNHCR) – የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኣካል (United Nations High Commission for Refugees)**
**ኣይ ሲ ኤን ዩ ኣር (ACNUR )– Alto Commissariato delle Nazioni Unite per i Rifugiati**
ኣድራሻ፡ via Alberto Caroncini, 19 – 00197 Rome
ስልክ፡ 06 802121
ፋክስ፡ 06 80212324
ኢመይል፡ itaro@unhcr.org

**ኦ ኣይ ኤም (OIM) – (Organizzazione internazionale per Migrazioni)**
**ኣይ ኦ ኤም (IOM) – የድፍን ኣለም ስደተኞች ማኅበር (International Organization for Migration)**
ኣድራሻ፡ via Nomentana, 62 – 00161 Rome
ስልክ፡ 06 44231428
ፋክስ፡ 06 4402533
ኢመይል፡ MRFRome@iom.int

- **ሃገራዊ**

**ሲ ኣይ ኣር (CIR) Consiglio Italiano per i Rifugiati**
ኣድራሻ፡ via of the Velabro 5/A – 00186 Rome
ስልክ፡ 06 69200114
ፋክስ፡ 06 69200116
ኢመይል፡ cir@cir-onlus.org

**(ARCI Nuova Associazione)**
**ክፍያ የማያስፈልገው የጥበቃ ስልክ ቁጥር፡ 800 905 570**
የጥገኝነት ጥያቄ ለማቅረብ መረጃ ወይም እገዛ ለማግኘት ከፈለጋችሁ፣ የጥገኝነት ጥያቄ ኣቅርባችሁ ከሆናችሁ ወይም የስደተኞች ፍቃድ ካላችሁ ወይም በሰብኣዊ ምክንያቶች የመኖሪያ ፍቃድ የተሰጣችሁ ከሆናችሁ ልትጠቀሙበት የምትችሉ ክፍያ የማያስፈልገው የስልክ ቁጥር ነው።
ኣድራሻ፡ via dei Monti di Pietralata, 16 - 00157 Rome
ፋክስ፡ 06 41609234
ኢመይል፡ itri@arci.it; nahum@arci.it

**ካሪታስ (CARITAS)፣**
ኣድራሻ፡ via delle Zoccolette, 19 - 00183 Rome
ስልክ፡ 06 6861554 – 06 6875228

ፋክስ፡ 06 6833295
ኢሜይል፡ area.immigrati@caritasroma.it

**አይ ሲ ኤስ (ICS) - Ufficio rifugiati di Trieste**
አድራሻ፡ via Roma, 28 34170 - TRIESTE
ስልክ፡ 040 3476377
ፋክስ፡ 040 3487592
ኢሜይል፡ icstrieste@yahoo.it

**አይ ኤስ ጂ አይ (ASGI) - Associazione Studi Giuridici on Immigrazione**
አድራሻ፡ via Gerdill, 7 - 10100 Turin
ፋክስ፡ 011. 4369158
ኢሜይል፡ segreteria@asgi.it
ወይ
አድራሻ፡ via Aquileia, 22 - 33100 Udine
ፋክስ፡ 0432.507115
ኢሜይል፡ info@asgi.it